

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ከማርች 31/2026 የነበረው

# የአየር ጠባይ ግምገማ እና

# በቀሪዎቹ ሁለት የበልግ ወራት የሚኖረው የአየር

# ጠባይ አዝማሚያ እና ምክረ ሃሳብ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

### 1. እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ የበጋ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

**አጠቃላይ**

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ወቅት ለሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ አካባቢዎች ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ ሲሆን፣ ለሰሜን ምስራቅ፣ ለመካከለኛዉ፣ ለምስራቅ፣ ለደቡብ ደጋማ አከባቢዎች እና ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል አካባቢዎች ደግሞ ሁለተኛ የዝናብ ጊዜያቸዉ በመሆኑ ለአርብቶ እና ከፊል አደሩ ለግብርና ስራ እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለዉ፡፡ የወቅቱ የዝናብ አጀማመር፣ መጠንና ስርጭት መስተካከል ለመጠጥ ዉሃ፣ ለእንሰሳት መኖ፣ ለእርሻዉ እና ለቆላማ አካባቢዎች የከባቢዉን የአየር ሙቀት ከማርገብ አንፃር ጉልህ አስተዋፅኦ አለዉ፡፡ በዚህ ጽሁፍ ያለፈዉ የበልግ ሁለት ወራት የአየር ጠባይ ግምገማና የቀጣዩ ሁለት ወራት አዝማሚያን ግንዛቤ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

ለዘንድሮ የበልግ ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ ከመስጠቱ አስቀድሞ በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ መካከለኛውና ምሥራቃዊ ክፍል ላይ ቀደም ባሉት ወራት የነበረውና በመጪዉ የበልግ ወቅት የሚኖረው የባህር ወለል ሙቀት ሂደት ላይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናት ተደርጓል፡፡ በበልግ ወራት የምስራቅና የመካከለኛዉ ፓስፊክ ዉቅያኖስ የላይኛዉ የዉሃ አካላት ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ (ENSO-Neutral) ክስተት ተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንደሚቀጥል እና የህንድ ውቅያኖስም ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ መሞቅ (Neutral-IOD) ስር ሊሆን እንደሚችል ተመላክቷል፡፡ በተጨማሪም በአትላንቲክ ውቅያኖስ ሰሜናዊ ክፍል እንዲሁም በሜዲትራኒያን ባህር ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የባህር ወለል መሞቅ እንደሚኖር ተጠቁሟል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በመጪው በልግ በሀገሪቱ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል መደበኛ ዝናብ፣ የቦረናና ጉጂ ዞኖች፣ የሲዳማ፣ የማዕከላዊና የደቡብ ኢትዮጵያ መደበኛና ከመደበኛ በላይ፣ በሌላ በኩል ሁለተኛ የዝና ወቅታቸዉ የሆኑት የደቡብ ትግራይ፣ የምስራቅ አማራ፣ አፋር፣ መካከለኛው እና የምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚኖር ተጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተመሳሳይ የምዕራብ አማራና የጥቂት የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሰሜናዊ ክፍል አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች

ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከመደበኛው አንፃራዊ መጨመር እንደሚኖረውም በትንበያው ተመላክቷል፡፡

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ እንዲሁም በግብርናው፣ በዉሃ ሴክተሮች እና በጤና ላይ አሳድሮ የነበረው የዳሰሳ እንዲሁም ወደፊትም ሊፈጥር በሚችለው ተፅእኖ ላይ ጽሁፍ ቀርቧል።

## ምዕራፍ አንድ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ


ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት (ከፌብሪዋሪ እስከ ማርች) 2026 በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የዝናቡ መጠን እና ስርጭት ቀስ በቀስ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የመጣበት ሁኔታ የነበር ሲሆን፤ በተለይም ከፌብርዋሪ ኢጋማሽ በኋላ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት የደመና ሽፋን እና ክምችት ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በማርች የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት ከተጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በመነሳት እርጥበታማው አየር ወደ ሀገራችን እንዲገባና በተለይም በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ስፍራዎቻቸዉ ላይ ከነበረዉ ጠንካራ እና የተሻለ የደመና ክምችት ጋር ተያይዞ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡበ ምዕራብ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በፌብርዋሪ እና በማርች ወር ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች ለመጥቀስም ያህል አዲስ አበባ ቦሌ 32.5፣ አርባምንጭ 36.6፣ 33.1፣ 32፣ አዋሳ 40.4፣ ቢሾፍቱ 33.4፣ ጎሬ 43.9፣ ጅማ 31.2፣ 47፣ 36.7፣ መተሃራ 69.4፣ ነገሌ 32.7፣ ነቀምት 34.4፣ ድሬ ዳዋ 31.6፣ 38.6፣ አቦምሳ 33፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 30.1፣ 32፣ አምቦ 33፣ አርጆ 46.4፣ 48.8፣ 34.2፣ አርሲ ሮቤ 36.5፣ አዋሽ አርባ 60፣ ባቲ 64፣ በደሌ 61.3፣ 32፣ 30፣ ብላቴ 34.5፣ 38፣ ቡኢ 31.5፣ 31.5፣ 45.3፣ 44.3፣ ቡሬ 33፣

ቡርጂ 68.4፣ 32.5፣ ጭራ 71፣ ጨዋቃ 50፣ ደብረ ብርሀን 37.2፣ ደምቢ ዶሎ 38.2፣ 41.2፣ ዲላ 38.1፣ ዶሎ መና 60፣ 50.8፣ ኢጃጂ 30.2፣ ፊቼ 37፣ 34፣ ገለምሶ 33.5፣ ገዋኔ 49፣ ወሊሶ 36፣ ጊኒር 80.4፣ 32፣ 44፣ ጊዳ አያና 31.1፣  ጉንዶ መስቀል 38.8፣ ሐረር 44.6፣ 61.8፣ ጅንካ 34፣ 41.7፣ 35.1፣ ኮንሶ 35.7፣ 31.8፣ 38.9፣ አዶላ 33.8፣ ሊሙገነት 32.7፣ 35.6፣ ማጀቴ 32፣ 60.5፣ ማሻ 30.4፣ 40.4፣ 40.6፣ መኤሶ 35.5፣ 148፣ 71.2፣ ሞያሌ 31.2፣ ምዕራብ አባያ 40፣ 33፣ ሳውላ 53.2፣ ኑራኤራ 81፣ ሰመራ 31.5፣ ሻዉራ 37.7፣ ሻምቡ 32.4፣ ተርጫ 44.2፣ 35.6፣ 30.4፣ ቴፒ 42.7፣ ጽጊቃ 31.4፣ 36.4፣ ወራቤ 43.1፣ 36.4፣ 40.9፣ 85.1፣ 43.6፣ 37፣ ወላይታ ሶዶ 37.5፣ መካነ ሰላም 35.8፣ ያቤሎ 37.6፣ 51.7፣ 37.4፤ 44.3፣  ባቱ 56.1፣ 43.9፣ አባጃራ 56.1፣ አዳሚ ቱሉ 31፣ 32.2፣ አጋሮ 34፣ አቃቂ 33.9፣ 42.9፣ አሺ 44፣ 54፣ አንጋጫ 35፣ አታንጎ 33.1፣ 44፣ 31.5፣ 31.5፣ በቆጂ 37፣ ቡልቂ 35.7፣ 37.4፣ 35.7፣ 34.2፣ 35.1፣ 36.9፣ 40.7፣ 34.8፣ 36.5፣ ቦሮዳ 35.6፣ ጨፌ ዶንሳ 84.2፣ መንደር 7 32.8፣ ደብረ ሲና 44.6፣ 33.1፣ 45.2፣ 43.2፤ 59.9፤ ደጋን 33.7፣ 44.5፣ ዲመካ 62፣ 33.4፣ 56.8፣ ጊዶሌ 31.7፣ 57.6፣ 31፣ 71፣ ጊናገር 31.8፣ 36.7፣ ጉሮ በቄሳ 30፣ ጉበቲ 47.7፣ ጎብዬሬ 34.2፣ ጎብዬ 45.6፣ ሃይቅ 51.5፣ ሃራ 36፣ 40፣ ሃሮ 30፣ 30.3፣ ሃንቲ 38.1፣ቀርሳ 30.5፣ 37.2፣ ቅዳሜ ገበያ 36.7፣ ኮበን 33.5፣ መቂ 73.7፣ መራሮ 35.8፣ መርሳ 48.2፣ መርጦ ለማሪያመ 42.5፣ ሞላሌ 63.7፣ ኦሞ ናዳ 33.4፣ 33.4፣ ኦንጋ 45.5፣ ሳጉሬ 33.7፣ ሳሃሉ 33.4፣ ተልተሌ 38.3፣ 38.3፣ 31.2፣ 38.2፣ 32.2፣ 41.2፣ 32.2፣ ተርኮዲ 36.1፣ ቱሉ ቦሎ 47.1፣ 37.6፣ መንደር 11 60፣ ያዮ 32.8፣ ይርጋ ጨፌ 32.2፣ 35.1፣ 50፣ 42.8፣ ዱባንቾ 35.6 እንዲሁም ደምበጫ 41.2 ሚ.ሜ ይገኙበታለ።

በአጠቃላይ ባለፉት ሁለት የበልግ ወራት በመቶ አርባ ስምንት (148) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30-148 ሚ.ሜ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡

Ethiopian Meteorology Institute





ምስል፡1 ከ ፌብርዋሪ 1 እስከማርች 31/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


ባለፈዉ የበልግ ወቅት አጋማሽ (ከፌብሪዋሪ እስከ ማርች) 2026 የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በልግ ዋነኛ እና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ቡኖ በድሌ፣ አርሲ፣ መዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ መዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖቸ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ ዳዋ እና ሊበን ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሃሪ፣ ማሂ፣ እና ፋንቲ ዞኖች፣ ከአማር ክልል የሰሜን እና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ፣ ዋግ ህምራ፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ ላይ ከ61-389 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ9-39 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ ባለፈዉ የበልግ ወቅት አጋማሽ (ከፌብሪዋሪ እስከ ማርች) 2026 የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር

ከኦሮሚያ ክልል ቦረና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ጉጂ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ቡኖ በድሌ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ድሬደዋ እና ሐረሪ፣ ከሶማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ ኖጎብ እና ኤረር ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሃሪ፣ ማሂ፣ ሃዉሲ እና ፋንቲ ዞኖች፣ ከአማር ክልል የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅ ጎጃም፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ፣ የቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ ክልል ዞኖች በአብዛኛዉ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡


በአጠቃላይ የበልግ ወቅት አጋማሽ ማለትም ከፌብርዋሪ እስከ ማርች ወራት የዘነበው የዝናብ መጠን በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ፤ በመካከለኛዉ እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተስፋፋ ዝናብ እንደነበረና በመጠን ረገድም ከ101-389 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ እንደተመዘገበ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሁለቱ ወራት ከሚጠበቀዉ መደበኛው የዝናብ መጠን ጋር ሲነጻጸር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ በሱማሌ ክልል፤ በጋምቤላ ክልል እና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከመደበኛው በላይ ዝናብ ተስተውሏል (ካርታ 3)፡፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ማለትም በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በአብዛኛዎቹ ቀናቶች ከ35 ዲ.ሴ በላይ ሆኖ መቆየቱ ተስተዉሏል፡፡




ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር


## 1.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የፌብሪዋሪ ወር በአብዛኛዎቹ የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በሲዳማ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በመካከለኛውና በምዕራብ ኦሮሚያ እንዲሁም በጥቂት የምዕራብ አማራ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የአፈር ውስጥ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የማሳ ዝግጅት ለማድረግ እና የተለያዩ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ የበልግ ሰብሎችን ለመዝራት አዎንታዊ ሚና እንደነበረው የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ለመጠጥ ውሃ እና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ሚና የነበረው ሲሆን፤ በተለይም ውሃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነበረ፡፡ በአንጻሩ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ ምሥራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረው አነስተኛ እርጥበት የእንስሳት መኖ እና የመጠጥ ውሀ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው፡፡


በሌላ በኩል በማርች ወር በቦታም ሆነ በመጠን የተስፋፋ የእርጥበት ይዞት እንደነበረ የተተነተኑ የአፈር ውስጥ እርጥበት አመላካቾች ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ወቅት ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ከማርች ወር ጀምሮ ለሚዘሩ የአጭርና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት፣ የማሳ ዝግጅት ለማድርግ እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። በአንፃሩም በብዙ ሥፍራዎች ላይ ተደጋጋሚነት ያለውከባድ መጠን ያለው እርጥበት በ24 ሰዓት ውስጥ የተመዘገበ ሲሆንና፤ ይህም ሁኔታ ውሃ አጠር ለሆኑት አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል፡፡ ነገር ግን በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል በጋሞ ዞን የአፈር መሸርሸና የመሬት መንሸራተት በመከሰቱ በሰዎችና በእንስሳት ህይወት እንዲሁም በሰብሎችና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል።

በአጠቃላይ በሁለቱ የበልግ አጋማሽ ወራት የነበረው ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት የማሳ ዝግጅት አስቀድሞ ለመጀመርና የበልግ ሰብሎችንም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት በቂ የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲኖር ከማስቻል አንጻር መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪም ይህ እርጥበት ለቋሚ ተክሎችና ለጓሮ አትክልቶች እድገት እንዲሁም ለእንስሳት መኖ እና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት መሻሻልና እርጥበት አጠር

በሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውሀ ለማሰባሰብና ለማከማቸት ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአጠቃላይ የወቅቱ የዝናብ ሁኔታ ለበልግ የግብርና እንቅስቃሴን ለማከናወን በአብዛኛው አዎንታዊ አስተዋጾ እንደነበረው ያሳያል፡፡ (ካርታ 4ሀ እና 4ለ) ፡፡




ካርታ 4ሀ፡ በፌብርዋሪ 2026 ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ4ለ፡ ማርች 2026 ወር የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የፌብሪዋሪ እና የማርች ሁለት ወራት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይሁን እንጂ በተከዜና በፊንጫ ተፋሰሶች ላይ ከመደበኛው በላይ የሆነ የውሃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። በፌብርዋሪ ወር ላይ በተወሰኑ የኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ ላይኛው እና መካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት የነበራቸው ሲሆን፣ ነገር ግን በጥቂት የታችኛው ኦሞ ጊቤና ስምጥ ሸለቆ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡


በተመሳሳይ መልኩ በማርች ወር የበልግ ዝናብ በመጠንና በስርጭት በሁሉም ተፋሰሶች የተሰፋፋ ሲሆን በደቡብ አጋማሽ በሚገኙ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ

ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ እና በዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እስከ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት የነበራቸው ሲሆን፤ በተጨማሪም በአብዛኛው መረብ ጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ በላይኛውና መካከለኛው ተከዜ፣ ኦጋዴን፣ የታችኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ በመካከለኛውና ታችኛውና አባይ፣ በላይኛውና መካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ከማሻሻል አንጻር ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም ከተገኘው ከባድ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ተፋሰሶች በተለይም ረባዳማና የወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች እንዲሁም በከተማ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ እና የወንዝ ሙላት ተከስቷል። በተለይም በኦሞ ጊቤ እና በስምጥ ሸለቆ አዋሳኝ ተፋሰስ በነበረው ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት በቦንኬ፣ ከንባ እና በጋሎ ባባ ወረዳዎች በሰው ህይወት እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት አስከትሎ ነበር (ካርታ 5 ሀ እና 5ለ)፡፡


## 1.4 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው ሁለት የበልግ 2026 ወራቶች በአብዛኛው የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የደቡብ፣ የደቡብ ምሥራቅ፣ የደቡብ ምዕራብና የሰሜን ምሥራቅ ዝናብ ተጠቃሚ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የነበረው የአየር ጠባይ ለወባ ትንኝ መራባት፣ መስፋፋትና ስርጭት ምቹ እንደነበረ የተተነተኑ የጤና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በዋናነት በማርች ወር ላይ የነበረው ምቹ የአየር ሁኔታ ለወባ መፈጠር እና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የነበረው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በምሥራቅ አማራ ደቡብ ወሎ እና ሰሜን ወሎ ዞኖች፣ በአፋር ክልል በዞን 3, 4 እና 1፣ በአብዛኛው የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ሀረሪ ክልል፣ እንዲሁም የሰሜን፣ የደቡብና የምዕራብ ሶማሌ ክልል ዞኖች ዝቅተኛ ምቹ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ነገር ግን በጥቂት የጋሞ፣ የጎፋ፣ የዳውሮ፣ የወላይታ እና የአፋር ዞን 3 አካባቢዎች ላይ ለወባ ትንኝ መፈጠርና መስፋፈት በመካከለኛ ደረጃ ስር የሚያርፍ ምቹ የአየር ሁኔታ እንደነበረ ለማየት ተችሏል (ካርታ 6ሀ)። በሌላ በኩል የነበረውን የአየር ሁኔታ በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ስንመለከት በአፋር፣ በሶማሌ፣ በአብዛኛው የኦሮሚያ ክልል ዝቅተኛ ቦታዎች፣ በጋምቤላ ክልል፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ እና በምዕራብ አማራ ዝቅትኛ ቦታዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ


ከፍተኛ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 6ለ)። በአንጻሩ የነበረው የአየር ሁኔታ በእንሰሳት ምርትና ምርታማነት እንዲሁም ጤንነት ላይ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረውም (ካርታ 6ሐ)::



ካርታ 6ሀ፡ የበልግ አጋማሽ ወቅት ለወባ ስርጭት ምቹ የሆኑ ቦታዎች




ካርታ 6ለ ፡ የበልግ አጋማሽ ወቅት ለሰዎች የነበረው የምቾት ሁኔታ





ካርታ 6 ሐ፡ የበልግ አጋማሽ ወቅት ለእንስሳት የነበረው የምቾት ሁኔታ

## 2. እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ


በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ወር የበልግ ወቅት የዝናብ ሥርጭትና መጠን በተለይም በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ከተቀሩት የበልግ ወራት አማካይ ዓመታዊ መጠን የተሻለ ድርሻ አለው። በሜይ ወር ደግሞ የዝናቡ ሥርጭት ከደቡብና ደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ቀስ በቀስ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ ይሄዳል።

በበልግ ወቅት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርጉት ዓለም አቀፍ ገጽታዎች መካከል በትሮፒካል የፓስፊክ ውቅያኖስ ምሥራቃዊ ክፍል ላይ የሚከሰተው የባህር ወለል ከመደበኛዉ በላይ መሞቅ (El Nino) ወይም ከመደበኛው በታች መቀዘቀዝ (La Nina) ነው። በመጪዎቹ ሁለት ወራት (ኤፕሪል እና ሜይ) አሁን በመታየት ላይ ያለው የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ከመደበኛው ጋር የተቀራረብ ( ENSO-neutral ) ክስተት ተጽዕኖ ሥር ሆኖ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም በሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የነበረው ከመደበኛ በላይ የሆነ የባህር ወለል ሙቀት (Positive - IOD) ሁኔታ እንደሚያሳይ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ስለሆነም በኤፕሪል ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች አንፃራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህም መሠረት በአብዛኛው የደቡብ ኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የሲዳማ ክልል፤ የመካከለኛ እና የምስራቅ ኦሮሚያ፤ የደቡብ እና የሰሜን ሶማሌ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ አካባቢዎች ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም የአፋር፤ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ፤ የምስራቅና የምዕራብ አማራ አካባቢዎች፣ የቤንሻንጉል ጉምዝና የዝናቡ መጠንና ሥርጭት መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ፡፡፡ በተጨማሪም አለፎ አለፎ በሚኖሩት ቀናት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል (ካርታ 7 እና 8)።





ካርታ 7 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-30/2026, የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር





ካርታ 8 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-30/2026, የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በሜይ ወር በመደበኛ ሁኔታ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ከበልግ አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ በመሄድ ከክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች መጠናከር ጋር ተያይዞ ዝናቡ ወደ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ይስፋፋል። በዚህም መሠረት በመጪው ሜይ 2026 የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል፣ የምስራቅ አማራ፣ መካከለኛውና የደቡብ ኦሮሚያ፣ከመደበኛው በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፣ የዝናቡ አወጣጥም በተወሰኑ ቀናቶች እንደሚዘገይ አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎዎ ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም የምዕራብ ኦሮሚያ፣ የአፋር ክልል፣ የደቡብ፣ መካከለኛዉ እና የምስራቅ ትግራይ፣ የምዕራብ አማራ አካባቢዎች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፣ የጋምቤላ ክልል፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል፣ መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል (ካርታ 9 እና 10)።




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-31/2026, የሚኖረወ የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር




ካርታ 10 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከሜይ 1-31/2026, የሚኖረወ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በአጠቃላይ በቀሪዎቹ ሁለት ወራት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ወቅታዊው ዝናብ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ ሁኔታ እንደሚኖርና በጥቂት ስፍራዎችም ላይ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናቶች የመኖር ዕድል አለው። በሌላ በኩል በሜይ ወር ከክረምት ዝናብ መጀመር ጋር ተያይዞ ምዕራባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል። በአጠቃላይ በቀሪዎቹ የበልግ ወራት አሁን በመታየት ላይ ካለውና ወደፊትም በተመሳሳይ መልኩ ሊኖር እንደሚችል በሚጠበቀው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የትሮፒካል ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት አንጻር መደበኛና ከመደበኛ በላይ ሁኔታ ሊቀጥል እንደሚችል ግንዛቤ ተወስዶበታል።

## 2.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የኤፕሪልና የሜይ ወር እርጥበት ለበልግ አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ከተቀሩት የበልግ ወራቶች አንጻር የሚስፋፋበትና የሚጠናከርበት ወር ነው። ይህም ሁኔታ ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የውሀ ፍላጎት መሟላትና እድገት እንዲሁም ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጥበት ወር ነው፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች ጎርፍ የሚከሰትበትና ለዘር በተዘጋጁና በሰብል በተሸፈኑ ማሳዎች ለይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልበት ወቅት ነው፡፡ እንዲሁም በሜይ ወር እርጥበቱ ከደቡብ፣ ከደቡብ ምሥራቅ፣ ከምስራቅና ከሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ቀስ በቀስ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ የረጅም ጊዜ ሰብሎች በስፋት በሚዘሩበት በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው።

በሚቀጥለው የኤፕሪልና ሜይ ወር ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተለይም ከማርች ወር መግቢያ ጀምሮ በተከታታይ ቀናቶች እርጥበት እያገኙ በነበሩ ስፍራዎች ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና፤ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለከብቶች መኖና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚጠበቀው መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ እርጥበት የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ በመሆኑ አርሶ አደሮች ተገቢ የሆኑ ግብዓቶችን በማካተት የእርሻ ሥራውን በተሟላ መልኩ ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከበልግ ዝናብ የመዋዠቅ ባህርይ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎች ተከታታይ ደረቃማ ቀናት በወሩ ውስጥ ሊከሰት ስለሚችል እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች ይህንን ሁኔታ ከግምት በማስገባት የሚገኘውን እርጥበት በማሰባሰብና በማከማቸት በመካከል ለሚከሰቱ ደረቅ ሰሞናት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በመጪዎቹ ሁለት የበልግ ወራት (ኤፕሪል እና ሜይ) በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሊኖር የሚችለው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለከብቶች መኖና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥርና በተጨማሪም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከአፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትም ሆነ በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የሚጠበቅ በመሆኑ አርሶ አደሩ ሊገኝ የሚችለውን እርጥበት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለወቅቱ የእርሻ ሥራ ተገቢ የሆኑ ግብዓቶችን በማካተት የእርሻውን ሥራ በተገቢ ሁኔታ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን እየጠቆምን ዝናብ አጠር አካባቢዎች ከበልግ ዝናብ የመዋዠቅ ባህርይ አንፃር ሊከሰት የሚችለውን የአፈር ውስጥ እርጥበት እጥረት ሊያግዝ በሚችል መልኩ የሚገኘውን እርጥበት የተለያዩ የውሃ ማቆያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በማሳዎች አካባቢ እንዲቆይ በማድረግ የአፈርን እርጥበታማነት እንዲጨምር በማስቻል የወቅቱን የእርሻ ስራ አመቺ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣዮቹ የኤፕሪል እና የሜይ ሁለት ወራት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት አብዛኛዎቹ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ያገኛሉ። በኤፕሪል ወር በአብዛኛው በኦሞ ጊቤ፣ በገናሌ ዳዋ፣ በዋቤ ሸበሌ፣ በስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለመስኖና ለሃይል ማመንጫ እንዲሁም የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ቢሆንም ከሚጠበቀው ከባድ መጠን ያለዉ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ተፋሰሶች በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ረባዳማና የወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች እንዲሁም በከተማ ቦታዎች ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊፈጠር ይችላል።

በሜይ ወር የሚኖረውን የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት በአብዛኛው በአባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆና የአዋሽ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ መጠን ያለው የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለውሃ ሀብት አጠቃቀም አዎንታዊ ሁኔታ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ በቀሪዎቹ ሁለት ወራት አብዛኞቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች የተሻለ የገጸ ምድር ውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ነገር ግን በአንዳንድ ተፋሰሶች በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የረባዳማና ወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች እንዲሁም በከተሞች ውስጥ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ይችላል። ስለዚህ በአንድ በኩል የውሃ ማከማቻና ጥበቃ ሥራዎችን ማጠናከር፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከጎርፍ አደጋ ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል። ስለሆነም የሚጠበቀው የአየር ሁኔታ በውሃ ሀብት ላይ ሊያሳድረው የሚችለውን አዎንታዊ ተጽዕኖ በሚገባ ለመጠቀም እንዲሁም ተያያዥ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የቀረቡትን ቦታ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በጤናው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣዮቹ የኤፕሪል እና የሜይ ወራት የሚኖረው የአየር ጠባይ በደቡብና ደቡብ ምሥራቅ እንዲሁም በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ እና በጥቂት የምዕራብ ሀገራችን ቦታዎች ላይ ለወባ መፈጠርና ስርጭት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል። በተጨማሪም የክረምት ዝናብ ቀድሞ የሚገባባቸው የምዕራብ የሀገራችን ቦታዎች ላይ ይህ ምቹ ሁኔታ እንደሚስፋፋ ይጠበቃል። በመሆኑም በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ዞኖች፣ የሲዳማ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልል፣ የደቡብ፣ የሰሜን እና የምዕራብ ሶማሌ ክልል ዞኖች፣ የጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፣ በጥቂት የምዕራብ አማራ ዞኖች፣ የደቡባዊ አፋር ክልል ዞኖች፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር እና የሀረሪ ክልል በቀጣዩ የበልግ ሁለት ወራቶች ላይ ወባ እና ሌሎች በትንኝ ለሚተላለፉ በሽታዎች ምቹ ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል የዴንጌ ትኩሳት በሽታ በድሬዳዋ፣ በአፋር፣ በሶማሌ ክልል ላይ ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ እንዲደረግ እና ማንኛውንም አይነት የቅድመ መከላከል ስራዎችን ማህበረሰቡም ሆነ የሚመለከተው አካል ማከናወን ያስፈልጋል። በሌላ በኩል የሚኖረውን የአየር ጠባይ በሰው ልጅ ጤንነትም ሆነ በእንሰሳት ምርትና ምርታማነት ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተጽዕኖ ስንመለከት፤ በተለይም በአብዛኛው የአፋር ክልል፣ ደቡባዊ ሶማሌ፣ የጋምቤላ ክልል፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና የምዕራብ አማራ ዝቅተኛ ቦታዎች ላይ አስጨናቂ የሙቀት ሁኔታ እንደሚኖር ይጠበቃል። በተጨማሪም በተወሰኑ የአፋር እና የሶማሌ ክልል ዝቅተኛ ቦታዎችን ላይ በእንሰሳት ጤና እና ተዋፅኦ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል።